| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምዳዊ ፡ ጽሑፍ ፤ "ሐተታ ፡ መጻሕፍት" |
| ርእስ ፤ | • በለጠ ፡ ገብሬ ፤ "በዕድሜ ፡ ጐዳና ፡ ላይ ፡ የጕዞ ፡ ትዝታ ። " |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | መስከረም ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፥ ቍ.2012-001 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |


# ሐተታ ፡ መጻሕፍት ፡፡

Books Review | revue de livres | مراجعة الكتب

---

በቅርቡ ፡ ከደረሱን ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡—

▶ **በለጠ ፡ ገብሬ** ፤ *"በዕድሜ ፡ ጐዳና ፡ ላይ ፡ የጕዞ ፡ ትዝታ ። "* ፥ ዐዲስ ፡ አበባ ፥ 2004 ፡ ዓ.ም. ፤ 266 ፡ ገጾች ።




ዛሬ ፡ የ 101 ፡ ዓመት ፡ የዕድሜ ፡ ባለጸጋ ፡ የኾኑት ፡ አቶ ፡ በለጠ ፡ ገብሬ ፥ ለ 20 ኛው ፡ ምእትያ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፥ ከፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ ወረራ ፡ እስከደርግ ፡ ዐምባ ፡ ገነን ፡ አገዛዝ ፡ ድረስ ፥ ምስክር ፡ የኾኑ ፥ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የመንግሥት ፡ ኀላፊነት ፡ ሀገራቸውን ፡ በቅንነትና ፡ በታማኝነት ፡ ያገለገሉ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ምሁር ፡ ናቸው ። የሕይወት ፡ ታሪካቸውን ፡ በወረቀት ፡ መዝግበው ፡ ካኖሩት ፡ በኋላ ፥ በልጆቻቸው ፡ ትጋት ፡ እንዲህ ፡ በጥራት ፡ ተሰናድቶና ፡ ታትሞ ፡ እኾላችን ፡ እጅ ፡ ገብቷል ። እመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ የትም ፡ የማይገኙ ፡ የታሪክ ፡ ማስታወሻዎች ፡ በጠራ ፡ አንደበት ፡ ተነግረውበታል ።

አቶ ፡ በለጠ ፡ ገብሬ ፥ በዚህ ፡ መጽሐፋቸው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ባለውለታነት ፡ አግኝተዋል ፡ ቢባል ፡ ማጋነን ፡ አይኾንም ። ኢትዮጵያ ፡ ዐዛውንትን ፡ አላጣችም ፡ ነበር ፤ ዳሩ ፡ ግን ፥ ሲደማመሩ ፡ ታሪኳን ፡ የሚሰጡንን ፡ የየግል ፡ ታሪካቸውን ፡ ስንቶቹ ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ መዝግበውላት ፡ ዐልፈዋል ፨ *"በዚህ ፡ ዐይነት"* ፡ ስንል ፥ የዱሮ ፡ ሰዎች ፡ ታሪክን ፡ ሲተርኩ ፥ በፍርድ ፡ አደባባይ ፡ ምሎ ፣ ተገዝቶ ፥ ከእውነት ፡ ሌላ ፡ አንዳች ፡ ሐሰት ፡ ወይ ፡ ዕብለት ፡ ሳይጨምር ፡ እንደሚመሰክር ፡ ምስክር ፥ ለትውልድ ፡ ስሕተትን ፡ እንዳያወርሱ ፡ ተጠንቅቀው ፡ ለማለት ፡ ነው ።

ከዚህም ፡ በላይ ፥ ያቶ ፡ በለጠ ፡ ገብሬ ፡ መጽሐፍ ፡ ዛሬ ፡ የማናያቸውን ፡ የዘመናቸውን ፡ ወግና ፡ ልማድ ፣ ደንብና ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፣ ድርስና ፡ ታሪክ ፤ በተለይ ፡ ደግሞ ፥ ባዔ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የነበረውን ፡ እውነት ፡ ፍንትው ፡ አድርገው ፡ ገልጠው ፡ አሳይተውናል ። መጽሐፉ ፡ የታሪክና ፡ የማኅበራዊ ፡ ጥናት ፡ መዝገብ ፡ የኾነውን ፡ ያኽል ፥ የሥነ ፡ ጽሑፍና ፡ የቴያትርም ፡ ማስታወሻ ፡ ነው ። ደራሲው ፡ በወጣትነታቸው ፡ ዘመን ፡ የስመ ፡ ጥሩው ፡ ባለቅኔ ፡ የቀኝ ፡ ጌታ ፡ ዮፍታሔ ፡ ንጉሤን ፡ ቴያትሮች ፡ በተዋናይነት ፡ ሠረተዋል ፤ የትም ፡ ተመዝግቦ ፡ የማናገኘውን ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፋቸው ፡ ዘክረው ፡ መዝግበውልናል ።

በዝግጅት ፡ ረገድ ፥ መጽሐፉ ፡ አንዳች ፡ የ *"ውጭ ፡ ተጽዕኖ"* ፡ ሳያርፍበት ፡ ተዘጋጅቶ ፡ በመታተሙ ፡ ዋጋውንና ፡ ክብሩን ፡ እጅጉን ፡ አሳድጎለታል ። ከማስታወሻዎቻቸው ፡ ከፊሉ ፡ በደርግ ፡ ዘመን ፡ በጸጥታ ፡ ኀይሎች ፡ ለምርመራ ፡ ተወስደው ፡ እንደጠፉባቸውና ፡ መጽሐፋቸው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ እንደተጓደለባቸው ፡ መቅድሙ ፡ ላይ ፡ ተነግሯል ። ተመሳሳይ ፡ አደጋዎች ፡ በሌሎች ፡ ቤተሰቦችም ፡ መድረሳቸው ፡ ይሰማልና ፥ ኹሉም ፡ በየበኩሉ ፡ ጠብቆ ፡ ያቈያቸውን ፡ ማስታወሻዎች ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ እያሳተመ ፡ ለታሪክ ፡ ሊያከማቻቸው ፡ ይገባል ። ምናልባት ፡ ያዘጋጆች ፡ ርዳታ ፥ ከይዘት ፡ ይልቅ ፡ በፊደል ፡ ጥንቀቃ ፡ ላይ ፡ ተወስኖ ፡ ኅትመቱን ፡ ሊያሻሽለው ፡ ይችላል ።

*"በዕድሜ ፡ ጐዳና ፡ ላይ ፡ የጕዞ ፡ ትዝታ ። "* ፡ የተባለውን ፡ የአቶ ፡ በለጠ ፡ ገብሬን ፡ መጽሐፍ ፡ ላንባብያን ፡ እጅጉን ፡ እንመክራለን ❖


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ።